## የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 804/2005 ለማሻሻል የተዘጋጀ የረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

**መግቢያ**

የአገራችን ብሔራዊ ደህንነትና ጥቅም እንዲያስጠብቁ ተልዕኮ ከተሰጣቸው ተቋማት አንዱ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ሲሆን መንግስት ባስቀመጠው የፀጥታና የደህንነት ተቋማት የሪፎርም አቅጣጫ መሰረት የተለያዩ የሪፎርም ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል። በዚህ መሰረት አገልግሎቱ የተቀመጠውን የሪፎርም አቅጣጫ ለማሳካት ጥናት አካሂዷል። በጥናቱ የተለዩ ክፍተቶችን በመቅረፍ ተልዕኮውን በሚፈለገው ደረጃ መወጣት በሚያስችል መልኩ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም የአገልግሎቱን አዋጅ ለማሻሻል በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ለረቂቅ አዋጁ ዝግጅት የተወሰዱ ግብዓቶች

ረቂቅ አዋጁን ለማዘጋጀት በአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የተካሄደ ጥናት፣በአገልግሎቱ አዋጅ ቁጥር 804/2005 የታዩ ክፍተቶችና በተግባር ያጋጠሙ ችግሮች፣ተዛማጅ የሆኑ የአገር ውስጥ የመረጃና ደህንነት ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ/ደንብ እና የተለያዩ አገራት የመረጃ ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች እንደ ግብዓት ተወስዷል።

### በረቂቅ አዋጁ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 የተካተቱት ድንጋጌዎች አስፈላጊነት አጭር ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በአገር ላይ የሚቃጡ የስነ ልቦና ጦርነቶችን የመመከት ሂደት በበላይነት ስለመምራትና ማስተባበር በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 7(7) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም በአገሪቱ ላይ የሚፈፀም የስነልቦና ጦርነት የመመከት ሂደት በአግባቡ ካልተመራ ብሔራዊ ደህንነትና ጥቅምን ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል። በመሆኑም በአገሪቱ የሚቃጣ የስነልቦና ጦርነትን ለመመከት ኃላፊነት ከተሰጣቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የመመከት ተግባራትን በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር ተቋም እንዲሆን በማስፈለጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት እና የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎትን ስለመምራትና ስለማስተባበር በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 7(8) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነት ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የአገሪቱን ብሔራዊ ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር የመረጃና የደህንነት ስራዎችን በሃላፊነት

የመምራት ስልጣንና ተግባር የተሰጠው ሲሆን የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት እና የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት የተልዕኮ ስምሪትም ሽብርተኝነትን፣የተደራጁ ድንበር ዘለል ወንጀሎችና ስደተኞችን መሰረት አድርገው ሊፈፀሙ የሚችሉ ወንጀሎችን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ከአገልግሎቱ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ስምሪት ያላቸው ተቋማት በመሆናቸው፤ከብሔራዊ ደህንነት ስጋቶች በተያያዘ ወቅታዊና አፋጣኝ የሆነ ምላሽ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች የተማከለ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በማስፈለጉና የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1264/2014 የተቋማቱ ተጠሪነት ለአገልግሎቱ እንዲሆን በመደረጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

የብሔራዊ ደህንነት ስጋቶችንና አደጋዎች ምላሽ አሰጣጥ ስርዓት በሃላፊነት ስለመምራትና ማስተባበር በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 7(9) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም አገልግሎቱ የአገሪቱ ብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮችን በበላይነት የመምራት ስልጣንና ተግባር የተሰጠው በመሆኑ በአገሪቱ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችና አደጋዎችን የስጋት ደረጃቸውን /threat level/ በመለየት ለሚመለከተው አካል ለማሳወቅና ስጋቱን ተከትሎ መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ የመፍትሔ ሃሳብ በማቅረብ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት በተደራጀ መልኩ የብሔራዊ ደህንነት ስጋቶችንና አደጋዎች ምላሽ አሰጣጥ ስርዓት በሃላፊነት የሚመራና የሚያስተባብር ተቋም እንዲሆን በማስፈለጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

አገልግሎቱ ከስራው ጋር በተያያዘ ብሔራዊ የመረጃ ማጠናቀሪያና ማከማቻ ቋት ስለማቋቋምና ማስተዳደር በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 7(10) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም ለመረጃ ትንተና፣ምዘናና ለመረጃ ደህንነት አጠባበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤የመረጃ ሚስጥራዊነት ደረጃ ለመስጠት፤መረጃዎች በሚስጥር የሚያዙበትን፣የሚጠበቁበትን፣ግልጽ ሊደረጉ የሚችሉበትን እንደአስፈላጊነቱም ከሚስጢራዊ ደረጃ የሚወጡበትና የሚወገዱበትን አሰራር ለመዘርጋት እና ከመረጃና ደህንነት ተቋማት የሚገኙ መረጃዎች ፍሰትና ስርጭት ማዕከላዊ እንዲሆን ለማድረግ በማስፈለጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

አገልግሎቱ ስልጣንና ተግባሩን ለመወጣት የሚያስችሉትን ድርጅቶች ስለማቋቋምና መቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 7(11) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም አገልግሎቱ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የመረጃና ደህንነት ስራዎችን በበላይነትና በኃላፊነት የመምራት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ የመረጃ ምንጩን በማስፋት ጥራት ያለው፣ተአማኒና ወቅታዊ የሆነ መረጃ ለማቅረብ ለዚሁ ተግባር የሚውሉ ድርጅቶችን በማቋቋም የአገልግሎቱን መረጃ የመሰብሰብ አቅም ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያግዝ በመሆኑ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

በብሔራዊ የደህንነት አጀንዳዎችና ስጋቶች ዙሪያ ግንዛቤ ስለመፍጠር በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 7(12) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም

አገልግሎቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በደህንነት ስጋት አጀንዳዎች ዙሪያ በህብረተሰቡ ዘንድ ብሔራዊ መግባባትን በመፍጠር ህብረተሰቡን የመረጃ ምንጭ ማድረግ በማስፈለጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (2) አገልግሎቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመቀናጀት የመረጃና የደህንነት ትንተና ውጤቶች የፍሰትና የስርጭት ስርዓት ስለማደራጀትና በበላይነት ስለመምራት በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 8(7) ሆኖ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም በመረጃና ደህንነት ተቋማት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የትንተና ውጤት ፍሰትና ስርጭት ማዕከላዊ በሆነ መልኩ ለሚመለከተው ውሳኔ ሰጪ አካል እንዲቀርብ ማድረግ በማስፈለጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (3) የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2)፣(3)፣(4) እና (5) ተሰርዞ (1) በጠቅላይ ሚንስትሩ የሚሾሙ ዳይሬክተር ጀነራል እና ምክትል ዳይሬክተር ጀነራሎች፣እና (2) አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል በሚል ንዑስ አንቀጾች እንዲተካ ተደርጓል።የነዚህ ንዑስ አንቀጾች ማሻሻያ አስፈላጊነት አዋጅ ቁጥር 804/2005 ስለአገልግሎቱ ምክትል ዳይሬክተሮች ጀነራሎች የሚገልጽ ድንጋጌ ያልነበረ በመሆኑና በአዋጁ የስራ ዘርፎችን ዘርዝሮ ማስቀመጡ የአገልግሎቱን ቀጣይ አደረጃጀት የሚያጠብ በመሆኑ ይህ ድንጋጌ እንዲሻሻል ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (4) የአገልግሎቱን የሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሥርዓት አጥንቶ ለመንግስት ስለማቅረብና ሲፈቀድ ተግባራዊ ስለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 12 (2) (ለ) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም የመረጃና የደህንነት የስራ ስምሪት የተለየ ዝግጁነትና የህይወት መስዋዕትነት የሚጠይቅ፣ የሙሉ ጊዜ ስራና የአገልግሎቱ ሰራተኞች ተቋሙ በሚመድባቸው ማንኛውም ቦታና ጊዜ የተሰጣቸውን ግዳጅ በአግባቡ የመወጣት ግዴታ አለባቸው። ከዚህ በተያያዘ ሰራተኞቹ ተጨማሪ ገቢ በሚያስገኙ ሌሎች ስራዎችን እንዳይሰሩ ገደብ የተጣለባቸው በመሆኑ በየጊዜው ከሚፈጠሩ የኑሮ ውድነት አንፃር በተልዕኮ አፈፃፀም ጫና እንዳይፈጠር ለማድረግ፣ተለዋዋጭ በሆኑ ሁኔታዎች ከሚፈጠር የስራ ስምሪት የሚመነጩ ጫናዎችን ለመቋቋምና አገልግሎቱን ብቃት ባለው የሰው ሃይል ለማደራጀትና ያለውን ሰራተኛ ለማቆየት እንዲሁም ሌላውን ወደ ተቋሙ እንዲቀላቀል ለማደረግ የተሻለ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፊያ ስለሚያስፈልግ የሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ሥርዓት በማስፈለጉ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5) ከአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ) ቀጥሎ "(ሐ) አገልግሎቱ ከሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች የሚገኝ ገቢ " በሚመለከት አዲስ ንዑስ አንቀጽ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም ተለዋዋጭ በሆኑ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች የመረጃና የደህንነት ስምሪትን በመንግስት በጀት ብቻ በሚፈለገው ደረጃ ለማከናወን የማይቻል መሆኑ፣ ዘመኑ ያፈራቸውን የመረጃና ደህንነት ቴክኖሎጂዎች ባለቤት በመሆን ጥራት ያለው መረጃና ማስረጃ ለማሰባሰብ የማይቻል መሆኑ እና የአገልግሎቱን አቅም ከመገንባት አንፃር በዕውቀትና በክህሎት የበለፀገና ተልዕኮውን በውጤታማነት መፈፀም የሚችል የሰው ሃይል ለመፍጠር፣ያሉትን ለማቆየትና ሌሎችንም ለመሳብ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ማሰደግ የሚጠበቅበት በመሆኑ ይህ አዲስ ንዑስ አንቀጽ እንዲካተት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (6) የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 804/2005 ከአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (1) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ከመረጃና ደህንነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ለደህንነት ስጋት ምንጭ ይሆናሉ ብሎ አገልግሎቱ ያመነባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ወይም ውስን አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዢ ሊፈጽም ይችላል።" በሚል እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነት የመረጃና የደህንነት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ በባህሪያቸው አስፈላጊ የሆነ ጥበቃ ካልተደረገላቸው በአገር ደህንነት ላይ ስጋት የሚፈጥርበት ዕድል ሰፊ ነው። አገልግሎቱ በቀጥታ ወይም ውስን አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዢ የማይፈፅም ከሆነ የተቋሙ አቅምና አሰራር ለሌሎች አካላት የሚጋለጥበት ወይም ተገማች የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር የሚችል በመሆኑ እና የሌሎች የመረጃና ደህንነት ተቋማት ልምድም ይህንኑ ስለሚያሳይ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (7) የአገልግሎቱ ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣ ደንብ መሰረት ስለመምራት በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 16 ቀጥሎ አዲስ አንቀጽ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነት የአገልግሎቱ የስራ ስምሪት የፓራ ሚሊተሪ ባህሪይ ያለውና የተለየ ዝግጁነት የሚጠይቅ የሙሉ ጊዜ ስራ በመሆኑ፤የአገልግሎቱ ሰራተኞች ልዩ ስነምግባር የሚጠበቅባቸውና ተቋሙ በመደባቸው ስራ፣ ቦታና ጊዜ ለመስራት የሚገደዱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከተቋሙ የስራ ባህሪይ የተነሳ የተለያዩ ግዴታዎችና ክልከላዎች የሚጣልባቸው መሆኑ፤አዲስ በሚቀጠሩና በነባር ሰራተኞች ላይ የደህንነት ማጣራት የሚደረግና የተለየ የምልመላ፣ የቅጥር፣ የሙከራ ጊዜ፤የዝውውርና የስንብት ስርዓት የሚያስፈልግና በአጠቃላይ የአገልግሎቱ ሰራተኞች የስራ ጫና ያገናዘበ የደመወዝ፣የጥቅማጥቅምና የህክምና አገልግሎት ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ለማስተዳደር የሚያስቸግር ስለሆነ ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (8) ከአገልግሎቱ አዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (5) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (6) “ማንኛውም የአገልግሎቱ ሠራተኛ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን ወይም በቅስቀሳ ላይ መሳተፍ ወይም መሰል ድርጊቶችን መፈፀም አይችልም።” በሚል እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነት አገልግሎቱ በህግ የበላይነት መርህ የሚገዛና የዜጎችን መሰረታዊ መብቶና ነፃነቶች በማክበር ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነትና ወገንተኝነት ነፃ ሆነው ተልዕኮን ያለአድሎ ለመፈፀም እንዲችል ለማድረግ በአገልግሎቱ ሰራተኞች ላይ ገደብ እንዲጣል በማስፈለጉ ነው።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (9) የአገልግሎቱ ሠራተኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው በስራው አጋጣሚ ወይም  በስራ ስምሪቱ ያወቃቸዉንና ያገኛቸውን ማናቸውንም መረጃ፣ ሰነድ ወይም ሪከርድ የተደረገ መረጃ ወይም ምንጭ ያለ ዳይሬክተር ጀነራሉ ፈቃድ መግለጽ የሚያስጠይቅ መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 804/2005 ያልተደነገገ በመሆኑ በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) ስር እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነትም አገልግሎቱን ከደህንነት ስጋት ነፃ ለማድረግ በስራው አጋጣሚና በስራ ስምሪት ከተቋሙ የስራ ግንኙነት ያላቸውን የአገልግሎቱ ሰራተኛ ያልሆኑ ሰዎችን ተጠያቂ የሚያደርግ ድንጋጌ እንዲያካትት ተደርጓል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (10) ማንኛውም ሰው ከአገልግሎቱ የተሰጠውን መረጃ ስለመጠቀምና ስራ ላይ ማዋል አለበት የሚል አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ከአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (2) ቀጥሎ እንዲካተት ተደርጓል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አስፈላጊነት በመረጃና ደህንነት ስራዎች አፈፃፀም በየደረጃ ካሉት ሌሎች አካላት የመተባበር ተግዳሮቶች የሚታይ በመሆኑና ስራዎች የሚፈፀሙት በሃላፊዎች መልካም ፈቃደኝነት ወይም ባላቸው ቅርበት በመሆኑ የመተባበር ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በአገልግሎቱ የሚሰጡ መረጃዎች ተግባር ላይ አለመዋላቸው እየተስተዋለ በመሆኑ ይህንን ግዴታ ተግባራዊ ያላደረገ አካል ተጠያቂ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ለመፍጠር ይህ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።